# እርምጃዎች

**ለመገናኘት እና በመግባባት ውስጥ ለመሳተፍ የሚረዱ እርምጃዎች።**

እነዚህ እርምጃዎች የተገነቡት እ.ኤ.አ. በ 2012 ከማህበረሰቦች ጋር ከተደረገው ጥናት ነው።

ኤጀንሲዎች ከማህበረስብዎ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ አስተያየት ወይም ግብረመልሶችን ያቅርቡ። መረጃ ልውውጦች ትክክለኛውን ግንዛቤ እንዲፈጥሩ በምን አግባብ መቅረብ እንደሚኖርባችው ሃሳብዎን ያቅርቡ።

በአደጋ ግዜ የሚተገበር የቤተሰብ/የማህበረስብ ዕቅድ ይኑርዎ።

እውቀትዎን ለማህበረሰብዎ ያካፍሉ

በማህበረሰብዎ ውስጥ ማን ተጨማሪ እርዳታ ሊያስፈልገው እንደሚችል ይገንዘቡ። እነዚህ ሰዎች ድጋፍ እያገኙ መሆናቸውንም ያረጋግጡ።



ለብዙሃን ጥቅም በሚል ተሳትፎና አበርክቶ ለማድረግ ፍቃዳቸውን ለሚስጡ ሰዎች እውቅናን ይስጡ።

ጎረቤትዎን ይተዋወቁ።

ከማህበረሰብዎ ጋር መልካም ግንኙነትን ይፍጠሩ።

በአካልም ሆነ በኢንተርኔት አማካኝነት በሚደረግ መደበኛ የማህበረስብዎ ስብሰባ አካል ይሁኑ።

ድጋፍ በሚያሻዎ ግዜ ጥሪ ማድረግ እንዲችሉ የማህበረስብዎ መሪዎችን እንዲሁም በአከባቢዎ በሚገኙ የመንግስት ኤጀንሲዎች የሚሰሩ ቁልፍ ሰዎችን ይተዋወቁ።

**አማርኛ | Amharic**
መጋቢት 2021 | March 2021
**www.cling.nz**

CLING Community Languages Information Network Group

**እነዚህ አስተያየቶች እርስዎና ማህበረሰብዎ የተለያዩ ጽሁፎችንና አገልግሎቶችን እንዴት በቋንቋዎ ማግኘት እንደሚችሉ ይጠቁማሉ**

ከመንግስት ኤጀንሲዎች ጋር ሲነጋገሩ መረጃን ማግኘት እንዲሁም አስተርጓሚ እንዲግኝ መጠየቅ መብትዎ ነው - አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ይህን አገልግሎት መጠየቅዎን አይዘንጉ።

አንዳንድ ጽሁፎች በቋንቋዎ ሊተረጎሙ ስለሚችሉ በድር ጣቢያዎች ላይ ኦፊሴላዊ (እውቅና የተሰጠው) መረጃ የት እንደሚገኝ ይወቁ ።





ከእንግሊዝኛ በተጨማሪ በሌሎች ቋንቋዎች ይዘት ስላላቸው የአከባቢዎን የማህበረሰብ መዳረሻ ሬዲዮ ጣቢያ ያዳምጡ።

እውቀትዎን ከማህበረሰብ ዎ ጋር ያካፍሉ



ከድርጅትዎ (የማህበረሰብዎ ድርጅት ካለ) ማህበራዊ ሚዲያ (ፌስቡክ ፣ ትዊተር ፣ ኢንስታግራም) ጋር ይገናኙ እንዲሁም የማህበረሰብ ጋዜጣዎችን ይፈትሹ

**ልብ ይበሉ መልካም ግንኙነት በዕለት ተዕለት ህይወት እንዲሁም በቀውስ ግዜ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።**